ማጠቃለያ

የዚያ ታላቅ ጀግና እና ፍፁም አይረሴ ሰው ሕይወት ባጭሩ ሲታይ ይህን ይመስል ነበር። ባሳለፍናቸው ምዕራፎች ውስጥ ይቅር ባይነቱን እና ዕናቱን፣ ጀግንነቱን እና ጥንቁቅነቱን፣ ዒባዳውን እና የነፃነት ተጋድሎውን፣ ጥንካሬውን እና ደግነቱን፣ መስዋዕትነቱን እና ጂሃዱን ለማየት ሞክረናል።

እንዲሁም የተበታተኑ ኃይሎችን ትክክለኛ ወደሆነው አመራረ እንዴት ማምጣት እንደቻለ እና ሁሉንም አገሮች ዳግም ወደ አንድነት አምጥቶ እንዴት አንድ ኢስላማዊ ግዛት ሊያደርጋቸው እንደቻለ አይተናል። ይህ አንድ የሆነ ጠንካራ አገር ከፍራንክች ፊት ቁም ሳይሆን ከመላው ምዕራብ ፊት በድፍረት መቆም ችሎ ነበር። የመስቀል ወራሪዎችን በአክሬ እና በያፋ አካባቢዎች ብቻ ታጥረው እንዲቀመጡ ማድረግ ችሎ ነበር። እሱ ካለፈ ከዓመታት በኋላ የሙስሊም ኃይሎች የመስቀል ወራሪዎችን አሸንፈው ከሁሉም የሙስሊም መሬቶች ተጠራርገው እንዲወጡ አደረጉ።

ሰላሑዲን ግዛቱ ተስጥሎ ሰሜን ኢራቅን፣ ኩርዲስታንን፣ ታላቋን ሶሪያ፣ ግብፅን እና ባርካህን ያካተተ ሠፊ ግዛት መሥርቶ እንደነበርም መጥቀሳችንን ይታወሳል።

ይህ ኢስላማዊ አንድነት ዕውን ሁኖ የተመለከተ ጊዜ ሙስሊሙ ዓለም ከዳር እስከ ዳር ፈነደቀ፣ በድል አድራጊነት ስሜት ተሞላ። ባጭር ጊዜ ውስጥ በጀግናው ሰላሑዲን ሥር የተንቀሳቀሰው ሠራዊት በየጦር ሜዳው የመስቀል ወራሪዎችን አንገት እያስደፋ ጉዞውን ቀጠለ ፡ ወሳኝ የነበረውን የሐቲንን ጦርነት በድል አጠናቀቀ። ትውልድ ሁሉ ሲዘክረው በሚኖረው በዚህ ድልም እየሩሳሌም ነፃ ወጣች። በወራሪዎች መዳፍ ውስጥ ቆሽሻ ከኖረች በኋላ ዳግም ነፃች።

ታሪክ ራሱን ይደግማል እንዲሉ ዛሬም የሙስሊሙ ዓለም ተከፋፍሏል። የመጨረሻው ኸሊፋ (የኦቶማን ኸሊፋ) ከወደቀ በኋላ የሙስሊሙ ዓለም በአይሁዶች እና በኢምፔሪያሊስቶች ሴራ ዳግም ተበጣጥሶ ወደ ትናንሽ አገርነት ተቀይሯል። በመከከላቸው ያለው

ልዩነት እና መከፋፈል በየዕለቱ ይጨምራል። በተቃራኒው ደግሞ ጠላቶቻቸው ያበልጥ አንድ ሲሆኑ እና ሲጠነክሩ ይታያል።

ዛሬ ሙስሊሙ ዓለም የሚገኝበትን ሁኔታ ዝም ብሎ ያስተዋለ ሰው ድሮ በመስቀል ወራሪዎች ሥር ከነበረበት ሁኔታ ጋር አንድ ሁኖ ያገኘዋል። ያው መከፋፈል፣ ያው የድሮው መጠላላት፣ ያው የድሮው ሐዘን፣ ያው የዚያን ጊዜው ሞኖና እና በደል ነፍስ ዘርተው እየተንቀሳቀሱ መሆኑን ይረዳል። ነገር ግን ያን ጊዜ ሙስሊሞች እንዴት እና ለምን ነበር የመስቀል ወራሪዎችን ድል ማድረግ የቻሉት? ቁም ነገሩ ይህን ጥያቄ መመለስ ነውና የሚከተሉትን ወሳኝ ነጥቦች ደግመን እናስታውስ፡-

- ያንጊዜ የታገሉት ኢስላማዊ መርሆዎችን ተከትለውና በኢስላም ስም ስለነበር ድል አድርገዋል ዛሬ ግን የሃሰት መፈክሮችን አንግበው ሲደክሙ ነው የሚታዩት።

- ያን ጊዜ የኢስላምን መመሪያዎች እና አስተምህሮዎች በቅጡ ተረድተው፣ በተግባርም ተርጉመውና ራሳቸውን ቀይረው ስለነበር ድል ማድረግ ችለዋል፣ ዛሬ ግን የምዕራቡ እና የምስራቁ አድናቂ ሁነው ማምጣት ከሚጠበቅባቸው አዕምሯዊና ልባዊ ለውጥ ተዘናግተው ይገኛሉ።

- ያን ጊዜ የእንድነትን ትልቅ ዋጋ ተረድተውና የሚገባውን ጥረት አድርገው ስለነበር ለድል በቅተዋል፣ ዛሬ ግን በትንሹም በትልቁም ምክንያት ተከፋፍለው በቀኝ እና በግራ ክንፎች ተሂድነዋል።

- ያን ጊዜ ከእነሱ የሚጠበቅባቸው ነገር ሁሉ ከፈፀሙ በኋላ በአላህ በመመካታቸው፣ ወደ እርሱ ብቻ በመጠጋታቸው እና ቃል ኪዳኑን ከልባቸው በማመናቸው ምክንያት ለስኬት በቅተዋል፣ ዛሬ ግን ተስፋ የሚያደርጉት ፍትህ የማያውቁ ምድራዊ ኃይሎችን ሁኗል።

- የአረብ እና የሙስሊም መሪዎች እንዲሁም የመንግስት ባለሥልጣናት ስኬታማውን መሪ ሳላሃዲንን መምሰል፣ አርዓያነቱን መከተል፣ ጥልቅ ዕምነቱን፣ ቁርጥ ውሳኔውን፣ ወደር የለሽ ጀግንነቱን፣ ትልቅ መስዋዕትነቱን፣ ብልሃት የተሞላበት የአፈፃፀም ችሎታውን እና ሌሎች መሰል መርሆዎቹን መከተል ይጠበቅባቸዋል። እንዲሁም ቀደምት ጀግና አባቶቻቸው በዋሉባቸው የትግል መስኮች ሁሉ እንዴት ድል ማድረግ እንደቻሉ፣ በበድር፣ በአልቃዲስያ፣ በአል-ያርሙክ፣ በሒቲን እና በዓይን ጃሉት ጦርነቶች እንዴት እንዳሸነፉ በጥልቀት ይገነዘቡ ዘንድ የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) የሕይወት ታሪክ ማጥናት እና ታሪክን ማንበብ ይኖርባቸዋል።

የአላህ ሕግ በውስጡ እውነትን፣ መልካምነትን እና ውበትን የያዘ መሆኑን እንዲያውቁ፣ ምሉዕ እና ለሁሉም ጊዜ እና ቦታ የሚስማማ መሆኑን እንዲረዱ፣ የጭንቅራ የድል እና የስልጣኔ አላማዎችን እንዲሁም የፍትህ፣ የሰላም እና የእኩልነት መርሆዎችን አጠቃሉ የያዘ መሆኑን እንዲገነዘቡ፣ የኢስላማዊውን ሕግ መርሆዎች እና የቁርአንን አስተምህሮዎች እንደገና ማጥናት ይኖርባቸዋል።

ጎያሉ አምላክ እንዲህ ብሏል፦

﴿ أَفَحُكْمَ ٱلْجَٰهِلِيَّةِ يَبْغُونَ ۚ وَمَنْ أَحْسَنُ مِنَ ٱللَّهِ حُكْمًا لِّقَوْمٍ يُوقِنُونَ ﴿٥٠﴾ ﴾

المائدة: ٥٠

"የማይደምነነትን ፍርድ ይፈልጋሉን? ለሚያረጋግጠም ሰዎች ከአላህ ይበልጥ ፍርዱ ያማረ ማን ነው?" (አል-ማኢዳህ፡ 50)

ሰላሑዲን መልዕክቱን በሚገባ አድርሷልና፣ ኃላፊነቱን በሚገባ ተወጥቷልና፣ የሙስሊሙን ዑማ ክብር መልሷልና ሙስሊሞችን አንድና ጠንካራ አድርጓልና፣ አየሩሳሌምን ከመስቀል ወራሪዎች ጥፍራማ እጅ እና በጥላቻ ከተሞሉ ኢምፔሪያሊስቶች ነፃ አውጥቷልና... አላህ ሥራውን ሁሉ እንዲቀበለው እንለምነዋለን።

ይህን ሁሉ ካልን በኋላ ስላሉዲን በምዕራብም ይሁን በምስራቅ ይህን ያህል ከፍተኛ ቦታ ቢሰጠው አይደንቅም፣ ስሙ ከሚለያን ሰምኛ እንደበት ባይጠሩ አይገርምም፣ ታሪክ መልካም ሕይወቱን፣ የመንፈስ ከፍታውን፣ ወደር ያልተገኘለት ጀግንነቱን፣ ሰብዓዊ ፍቅሩንና ክብሩን እንዲሁም ያላሰለሰ ጥረቱን በደማቅ ቀለም ዘግቦ ቢያስቀረው እንግዳ ነገር አይሆንም።

አሁን የቀረን ነገር ቢኖር የልብ ወዳጁና ጓደኛው ያደረገለትን ዱዓ እኛም ደግመን ማድረግ ብቻ ነው "አላህ ሆይ ለዲንህ ድል ለማምጣት ከልቡ መልፋቱን እና ፍቅርህን ፍለጋ ሲታገል መኖሩን ታውቃለህና በፍቅርህና በምህረትህ ተቀበለው።"

አሚን!!